# ድንቄም ጋዜጠኛ፤ ብርቄም ኦዲተር

ከብርሃኑ ተሰማ

ፈላስፎች እንዳሉት የሰው ቁምነገሩ ደሙ ወንይም ፅሙ ሳይሆን ማህበራዊ ግንዛቤው ነው። ይህ ማህበራዊ ግንዛቤ ደግሞ በአግባቡ ሥራ ላይ ካልዋለ ዋጋቢስ ይሆናል። ችግርን መፍታት መቻል አንደኛው የግንዛቤ ሂደት ሲሆን ዛሬ የቅንጅት መሪዎች ሽኩቻ ሰበብ ቡድኖች እያሳዩ ያሉት ባህሪዪና ፀባይ ተቀባይነት የማይኖረው ከዚህ ማህበራዊ ግንዛቤ ውጪ የሚሆን ነው።

ለዚህ አጭር መጣጥፍ ያነሳሳኝ በኢ አም አፍ (EMF) "የሻለቃ ቅሌት (corruption) ለቅንጅት መከፋፈል ምክንያት ነው" ብሎ ማቅረቡ በጣም ግርሞኝ ነው። ጋዜጠኛ ሲባል በሃቅ ላይ ተሞርኩዞ በቂም በቀል ሳይሆን የሁኔታዎችን ትክክለኛነት መርምሮ ለማንኛውም መሳሪያ ሳይሆን እውነቷን ለሕዝብ የማቅረብና ሥነ ምግባር(ethics) የታከለበት የሥራ ዘርፍ ነው። ለጋዜጠኝነት ሙያ; ነባራዊነት ጠቃሚ መመሪያው (significant principle) ነው። Online Dictionary የጋዜጠኝነት ሙያ ነባራዊነትን እንደሚከተልው ይገልፀዋል። "According to scholars, objectivity may refer to *fairness*, disinterestedness, factuality, and nonpartisanship…" በዚህም መሰረት "they are often expected to report in the most objective and unbiased way to serve the public good." ይላል።

ታዲያ እንደዚህ ባለው ሙያ ሕዝባዊ አገልግሎት መሰጠት ያለበት በጥሩ ሥነ ምግባር ላይ ተመርኩዞ፤ በግል አስተያየትና አመለካከት (ideology) ሳይጠመዱ መሆን ይገባዋል። ይህ ሳይሆን ቀርቶ ግን የራስ ፍርድ አስጣጥ በሌላ ኃይል ተፅዕኖ የሚደረግበት ከሆነ ያ አስተሳሰብ ነፃ ወይንም ነባራዊ መሆኑ ቀርቶ ስሜታዊ ይሆናል። ስሜታዊ ሲሆን ደግሞ ሓቅን የመካድ መስመር ይከተላል። ይህም ደግሞ የጠነከረ ውይይትና ክርክር ድጋፍ ካልኖረው በራሳችው ቅድመ-ፅንስ (preconceived) አስተሳሰብ ውስጥ በመዘፈቅ አመለካከታቸውን የሚያንፀባርቅ ይሆናል። ሰዎች በባህሪያቸው ፋክክር የሚሹና ለውጤቱ የሚጓጉ ፍጥረታት ናቸው። በሁኔታዎች ላይ ተመስርተው አሸናፊ ሆነው ለመገኘት የማያደርጉት የማይወጡት አቀበት የለም። በዚህ ሂደት ላይ ነው አንዳንዶቹ የሌላውን መብት የሚገፉት፤ ወይንም በሚያደርጉት የተሳሳተ መንገድ የራሳቸውን አስተሳሰብ የምታቀቡት፤ ወይንም ለሂስና ግለሂስ የሚዳረጉት። ይህን ሁሉ በአመክሮ የተመለከተ ብቻ ነው ሕዝባዊ አስተሳሰብ የሚኖረው።

የቀለም ትምህርት ብቻውን ለሕዝባዊ አስተሳሰብ መጎልበት ዋስትና አይኖረውም። ትምህርት ሲባል አካዳሚክ ትምህርት ብቻውን ያፈነገጠ አስተሳሰብ (divergent thought) ሊያስከትል ስለሚችል የሎጂክ መድብል እንዲኖረው ይፈልጋል። ትምህርት ዕውቀት የመቅሰሚያ አዎንታዊ አገማመትና ጥበብን የማሳደጊያ ሂዳት ነው። ይህም የሚጀምረው ገና በውልደት መሆኑን አብዛኛዎቹ ያምኑበታል። ታድያ አካዳሚክ ትምህርት የቀሰመ ሁሉ; ሁሉን ያውቃል ማለት አይቻልም። እንዲያውም በአንድ ሙያው የተካነ ግለሰብ ለሌላው ባዕድ ሊሆን ይችላል። እንግዲህ ይህንን ነው መረዳት ያለብን። በሙያዬ የሰለጠንኩ ነኝ በማለት ብቻ ከራስ በላይ መኩራትና እኔ ያልኩት ብቻ ትክክል ነው፣ ተቀበሉኝ፣ ተከተሉኝ አለበለዚያ ትረገማላችሁ ብሎ ማለት ግብዝነት (hypocrisy) ነው።

እንግዲህ በኢ. አም አፍ (EMF) ላይ ከኦዲትር አቶ አስማማው ጋር ውይይት ሲያደርጉ የነበሩት ጋዘጤኞች፣ በኔ አመለካከት የጋዜጠኝነትን ሥነ ምግባር (Ethics) አልተከተሉም። እነኝህ ጋዜጠኞች ከበስተጀርባቸው እውነት ለቅንጅት ሕልውናና መጠናከር አስበው ነው ወይስ አጠቃላይ ሕልውናውን ለማዛባት? በጣም የሚገርመው በሻለቃ ላይ ያላቸውን ጥላቻ ሳያውቁም ሆነ / እያወቁ በፓርቲው ላይ ማንፀባረቃቸው ነው። በጋዜጠኝነት ሙያቸው ማመዛዘን የነበረባቸው (ምንም እንኳን በግላቸው የአንድ ቡድን ደጋፊ ቢሆኑም) በቃለ ምልልሱ ያገን ማሳየት አልነበረባቸው። ጥያቄም ሲያቀርቡ ራሳቸው መስማት የሚፈልጉትን ሳይሆን ሕዝቡ መስማት ይፈልጋል ብለው መሆን ነበረበት። ሕዝቡ ማወቅ የሚፈልገው የአንድ ወገን ብቻ ወይም ወገንተኝነትን ሳይሆን በሁለቱም በኩል ምን ችግር እንዳለ ነበር። ይህም በመሆኑ ፕሮግራሙ የአንድ ቡድን ቃለ አቀባይ ጥያቄና መልስ የመሰል ነበር።

ከዚህም በተጨማሪ የአንድ ግለሰብ በድርጅት ውስጥ ያለውን ሚና በወግ የተረዱት አይመስለኝም። በኢ. አም አፍ ድህረ ገፅ ላይ "ለቅንጅት መከፈል ምክንያት የሻለቃ ዮሴፍ ምዝበራ ነው። (Shaleka Yosef's corruption - Reason for Kinijit's division)" ሲሉ:

እውነት ቅንጅት በአንድ ሰው ያውም በከፍተኛ አመራር ውስጥ ምንም ሚና ባሌለው ግለሰብ ሊከፋፈል የሚችል ፓርቲ ነው?

ታዲያ እንደዚህ ብለው የሚያምኑ ከሆነ ቅንጅት ሕዝባዊ መሠረት አለው፤ ቅንጅት መንፈስ ነው ማለቱ ለምን አስፈለገ። ቅንጅት እንደ "የእንቧይ ካብ" የአንድ እንቧይ መጉደል በቀላሉ ካቡን የሚንድ ነው ማለቱ ይቀል ነበር። ቅንጅት ግና ከዛ የበለጠ ጠንካራ መሆኑን በ1997ቱ ምርጫ መመልከት ተችሏል። እንደ ጋዜጠኛ ሥነ ምግባር የሁኔታዎችን ነባራዊነት አመዛዝነው ሪፓርት ማቅረብ ሲገባቸው ሻለቃን ሰበብ እነሱም ቢሆኑ ድርጅቱን በሚጎዳ አሉባልታ ላይ መሰማራታቸውን መረዳት ነበረባቸው። ወገናዊ ከሆኑ ደግሞ ማገልገል የሚችሉት ሰፊውን ሕዝብ ሳይሆን የተወሰነውን ክፍል ብቻ ነው። ያ ደግሞ በበኩሉ የሚቀርበውን ዜና የተውገረገረ ያደርገዋል።

ከሁሉም በላይ ግን የኦዲተሩ አሰራር ከሥነ ምግባር የራቀ (unethical) ከመሆኑም በላይ አሳፋሪም ነበር።

ለመሆኑ ምን ዓይነት ኦዲተር ነው ገንዘብ ያዥ ሳይዝ ሌሎቹን አባላት ሊመርምር የሚለው? ገንዘብ ገቢ ሲሆን ወደ ገንዘብ ያዡ ያልፋል፣ ይመዘገባል፤ ሂሳብ ሹም ካለ የገባው ሂሳብ በትክክል መግባቱን ይከታተላል። በሌላ በኩል ደግሞ ወጪ ሲሆን በሚመለከተው ተጠይቆ ከፀደ በኋላ ወጪ ሆኖ ለሚመለከተው ይከፈል። ከተጠያቂነት ለመሸሽ ምናልባት ፎርማል የሆነ አሰራር የለንም የሚል ሃሳብ ሊኖር ይችላል። ይህ ተቀባይነት አይኖረውም። ፖለቲካ አመራር እየሰጠን ነው እየተባለ ቀላል የሂሳብ አሰራር የለንም ማለት መቀለድ ይሆናል።

በዚህም መሰረት ኦዲተሩ ሻለቃን መረመርኩት የሚሉት ይኸን ያህል ገንዘብ ባከነ ሲሉ፥ በመጀመሪያ ደረጃ ከየትና እንዴት ገባ? በማንስ እጅ ገቢ ሆነ? እንግዲህ ገንዘቡ በገቢነት በገንዘብ ያዡ ካልተመዘገበና በኋላም መጠኑ ካልታወቀ ይህን ያህል ባከነ ለማለት አስቸጋሪ ነው። ለመሆኑስ (በጣም ትልቁ ጥያቄ) እስከዛን ጊዜ ድረስ ሻለቃ ብቻ ነበር  ገንዘብ ለሥራ ማስኬጃ ወጪ አድርገው ሥራ ላይ ያዋሉት? በሌሎች በኩል ምንም ወጪ የለም? የተረከቡት የለም? ወይንስ አውራርደዋል? ምነው ኦዲተሩ በያንዳንዱ አመራር ስም ወጪ ሆኖ ያልተወራረደውን  ወይንም የተወራረደ ሂሳብ መመልከት አቃታቸው? ያ ቢሆን ኖሮና ሌሎች አባላት ተመርምረው ነፃ ሆነውና የሻለቃው እንቢተኛ ቢሆኑ፣ ጉዳዩ አጠያያቅ በሆነ ነበር። እርግጠኛ ነኝ KIL ከሚሊዮን በላይ ገንዘብ አሰባስቧል። ምነው ታዲያ ይህ ሁሉ ውዝግብ በ$250,000 ላይ ብቻ ሆነ? ኦዲተሩስ ምነው ስለቀሪው ሂሳብ ዝምታን መረጡ?

ይህ ነው እንግዲህ የጥረጣሬ መነሻ የሆነው። አንድ ኦዲተርስ ምርመራውን ሳያጠናቅቅ እንዴት ሕዝብ ፊት ቀርቦ አንዴ ሚሊዮን የሚጠጋ ገንዘብ በሻለቃው ባከነ ሲሉ ፤ በሌላ ጊዜ ደግሞ ገንዘቡ አልጠፋም ግን ወደ ሌላ የባንክ ሂሳብ ተወሰደ ማለት ጀመሩ። ምነው በመጀመሪያስ ደረጃ ስሌቱ መጨረሻ ሳያደርሱ አደባባይ መውጣት መረጡ? በቃለ ምልልሳቸው እንደተሰማው እንደውም ማንም ስለኔ ከተናገረ እከሳለሁ እያሉም ይዝቱ ነበር። ትክክለኛውን ገቢና ወጪ ሰርተው ወይንም መስራት ካልቻሉ ፡ ያልቻሉበትን ሪፓርት ለኮሚቴው አቅርበው ኮሚቴው ሕጋዊ እርምጃ መውሰድ ሲገባው፣ ገንዘቡ ባከነ እንደገና አልባከነም ግን ሂሳቡ ተቀየረ ማለት ትክክለኛ ሥነ ምግባር አይሆንም።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኖራለች!!!